
# ቅኝት

## ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ

### ውልደትና ዕድገት

በፍቃዱ ኃይሉ፣ቅ/ማ/ዩ/ኮ



***መንደርደሪያ***

*“ዐዋጅ፡፡*

*ሞኣ አንበሳ ዘ እምነገደ ይሁዳ፡፡*

*ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፡፡*

*እስካሁን ማንም የእጅ ሥራ አዋቂ የነበረ ሰው በውርደት ስም ይጠራ ነበር፡፡ ስለዚህም ማንም ሰው ለመማርና ለመሰልጠን የሚደክም አልነበረም፡፡ በዚህ ጎጂ በሆነ ሁኔታ ብንኖር ቤተ ክርስቲያኖች ይዘጋሉ፡፡ ይልቁንም ክርስቲያን አይገኝም፡፡*

*“በሌሎች አገሮች እያንዳንዱን ነገር ብቻ መማር ሳይሆን፥ አዲስ ነገሮችም ይሰራሉ፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ለወደፊት ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ሁሉ ከስድስት ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን፡፡*

*“ልጆታቸውን ለማስተማር ለማይተጉ ቤተሰቦች፥ ወላጆታቸው ሲሞቱ ንብረታቸው ለልጆታቸው መሆኑ ቀርቶ ለመንግስት ይተላለፋል፡፡ ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን የሚያዘጋጀው መንግስቴ ነው፡፡”*

በ18ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የተነገረው ይህ አዋጅ በጥቅሉ ለዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ፋና ወጊ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ በወቅቱ ዘመናዊ ትምህርት ትውፊታዊ የኦርቶዶክስ ትምህርትን ያጠፋል የሚል ስጋት በቀሳውስቱ እና በምዕመኑ ዘንድ ስለነበር፥ ዳግማዊ ምኒልክ ‘ክርስትና እንዳይጠፋ’ የሚል ማግባቢያ በአዋጃቸው ውስጥ የግድ ማካተት ነበረባቸው፡፡

ስለዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ እንዴት ተወልዶ ዛሬ ላይ እንደደረሰ ስናወጋ፥ እግረ መንገዳችንን የጥንታዊውንና መካከለኛውን ዘመን ትምህርት ምን እንደሚመስል ማውራታችን አይቀርም፡፡ ከዚያው እንጀምር፡፡

### ትውፊታዊ ትምህርት በኢትዮጵያ

ሪቻርድ ፓንክረስት “የቤተክርስቲያን ትውፊታዊ ትምህርት (traditional education) የሚጀምረው በድምጽ በተፈጠሩ፣ እያንዳንዳቸው ሰባት ርቢ ባላቸው 26 ፊደላት ቆጠራ ሲሆን ‘መልዕክተ ዮሃንስ’ በመባል የሚታወቀውን ጽሁፍ ማንበብ ከፊደል ቆጠራ ተከታዩ እና የመጀመሪያው ደረጃ ነው፡፡” ሲሉ ፅፈዋል፡፡ ከዚያ ጽህፈት ይከተላል፣ በሦስተኛ ደረጃ የሐዋርያት ሥራ ጥናት፣ ጸሎት እና የሒሳብ ስሌቱ ይቀጥላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ትውፊታዊ ትምህርት የተወለደው ከ3,000ዓመት በፊት እንደሆነ ይነገራል - የዳበረው ደግሞ ክርስትና ወደኢትዮጵያ መግባቱን ተከትሎ ነው፡፡

የግዕዝ ፊደላት የጥንታዊ ሳባ ግዛት ከነበረችው ደቡብ አረቢያ ስልጣኔ የተወረሰ /እያደገ የመጣ/ እንደሆነ አንዳንድ ታሪካዊ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ ፊደላቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት 2,000 ዓመታት ቀደም ብለው የተፈጠሩ እንደሆነ ቢነገርም፥ በኢትዮጵያ የግዕዝ ትምህርት በሰፊው የተጀመረው ግን በንጉሥ ኢዛና በኩል ኢትዮጵያ ክርስትናን ከተቀበለችበት ከአራተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ትውፊታዊ ትምህርት ውስጥ የሒሳብ ስሌቶች እንደነበሩ የሚገምቱ ወይም የሚያውቁ ጥቂቶች ናቸው፡፡ ሆኖም የቀን አቆጣጠርን በተመለከተ ብቻ እጅግ ውስብስብ የሆኑ ትውፊታዊ ስሌቶች እስካሁንም ድረስ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ውስጥ አሉ፡፡

በዘመናዊ የሒሳብ ቀመሮች የምናውቃቸው ስሌቶችን (በተለይም ማባዛትን እና ማካፈልን) በተመለከተ ፖውል ሬኒ የተባሉ ተመራማሪ "Ancient Numerals and Arithmetic" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፋቸው የጥንታዊ ግብፃውያን፣ ኢትዮጵያውያንና ባቢሎናውያን የሒሳብ ስሌቶችን ተንትነዋል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ኢትዮጵያውያን ይጠቀሙበት የነበረው ስሌት ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ ሲሆን ለዘመናዊው የሒሳብ ስሌት ፈር ቀዳጅ እንደሆነ ተጠቅሷል፡፡ የጥንታዊ ኢትዮጵያውያን የሒሳብ ስሌቶች ዜሮን ስለማያካትቱ፥ እንደ ፖውል ሬኒ "ምንም እንኳን የግብፃውያኑ የማባዛት ስሌት የተሻሻለ ቢሆንም፥ የኢትዮጵያውያኑ ቀለም ላይ ተመስርቶ ያደገ ሳይሆን አይቀርም፡፡"

ይሁንና እነዚህ ለዘመናዊ ትምህርት መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ ትውፊቶች ከትውልድ ትውልድ ሊሸጋገሩ አልቻሉም፡፡ እንዲያውም ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ ያቆጠቆጠው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ ላይ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ ለዚህ እንደዐቢይ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የሚገምታቸው መንስኤዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፡-

- ዘላቂ አደረጃጀት የነበራቸው የትምህርት ተቋማት አለመኖራቸው፣ (ይህም በተለይ እ.ኤ.አ. በ969ዓ.ም የተመሰረተው የግብፁ አላዛር ዩንቨርስቲንና በ1026ዓ.ም. ተመስርቶ እስከዛሬ መዝለቅ የቻለውን የኦክስፎርድ ዩንቨርስቲን ስንመለከት ጥንታዊ ዕውቀትን ለዘመናዊው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚኖራቸውን ድርሻ መረዳት እንችላለን፡፡)
- ተደጋጋሚ ጦርነቶች መበራከታቸው፣ (ጥንታዊት ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ንግሥናን በማስከበር፣ ግዛትን በማስፋፋት እና አንዳንዴም በሃይማኖታዊ ምክንያቶች ሳቢያ የእርስ በእርስ ጦርነቶችን እንዲሁም ከውጭ ወራሪዎች ጋር ጦርነቶችን አካሒዳለች፡፡ እነዚህ ጦርነቶች ትውፊታዊ ትምህርቶችን እንዳይስፋፉ፤ ይልቁንም እንዲወድሙ ምክንያት ሆነዋል፡፡)

**ዘመነ አስኳላ**

የ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ኢትዮጵያ ከትውፊታዊው የቤተክርስቲያን ትምህርት፣ በወቅቱ አስኳላ የሚል ስያሜ ወደተሰጠው ዘመናዊ ትምህርት ለመሸጋገር ዳዴ ማለት የጀመረችበት ወቅት ነው፡፡ አፄ ቴዎድሮስ (ዳግማዊ) ጋፋት ላይ አሁን በተደራጀና በዘመናዊ መልኩ የቀረቡትንና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና የምንላቸውን የመሰለ፥ የወጣቶች ማሰልጠኛ የመክፈት ሕልም ነበራቸው፡፡ ምንም እንኳን ዋነኛው የንጉሡ ዓላማ የጦር መሳሪያ ማምረት ቢሆንም፥ በዘመናዊ መልኩ የተደራጀ ማሰልጠኛ ለመክፈት በማሰብ ግን ታሪክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሲል ይዘክራቸዋል፡፡ ያም ሆኖ በወቅቱ ከነበረው የተዛባ ባሕላዊ አስተሳሰብ የተነሳ፥ ማሰልጠኛ ይቋቋምበታል ተብሎ በታለመው ጋፋት በጦር መሳሪያ ምርት እንዲሳተፉ የተደረጉት የተገለሉት እና ‹ቀጥቃጭ/ሞረቴ/ቡዳ› በሚል ቅጽል ስም ተለይተው የሚታወቁት ኢትዮጵያውያን ብቻ ነበሩ፡፡

ከዚያ በኋላ ባሕሩ ዘውዴ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው መፅሃፋቸው ላይ እንዳስቀመጡት "የመደበኛ ትምህርት በኢትዮጵያ መስፋፋትን በተመለከተ በምኒልክ ዘመነ መንግሥት ፍጻሜ አካባቢ አንድ ዐቢይ ድርጊት ተከናውኗል፡፡ ይህም በንጉሠ ነገሥቱ ስም የሚታወቀው ትምህርት ቤት በ1900ዓ.ም. መከፈቱ ነው፡፡"

ዳግማዊ ምኒልክ ይህንን ያድርጉ እንጂ መንገዱ ሁሉ ጨርቅ ሆኖላቸው ነበር ማለት አይቻልም፡፡ በወቅቱ ዘመናዊ ትምህርት ሃይማኖትን ያጠፋል የሚል ስጋት ስለነበር፥ ኢትዮጵያን በሃይማኖት ትመስላት ከነበረችው ከግብፅ መምህራንን ማስመጣት የግድ ነበር፡፡

ከግብፅ የመጡት መምህራን ከኢትዮጵያውያኑ ተማሪዎች ጋር የቋንቋ መግባባት ችግር ነበረባቸው፡፡ ይህንኑ ተከትሎ መምህራኑ ተጋራፊዎች በመሆናቸው ብዙዎቹ ተማሪዎች (የተቀማጠሉ የመኳንንት ልጆች እንደመሆናቸው) ትምህርታቸውን እየጠሉ እቤታቸው መቅረት ጀምረው ነበር፡፡ ይህንን የታዘቡት ዳግማዊ ምኒልክ ለያንዳንዱ የመሳፍንት ቤተሰብ የተማሪዎቹን ስም ዝርዝር እያስፈሩ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እስከመጻፍ ደርሰው ነበር፤ ያውም በዕድሜያቸው ማክተሚያ ሰሞን ደብረሊባኖስ ለፀበል በተቀመጡበት ወቅት፡፡ መኳንንቱም በበኩላቸው የንጉሡን ትዕዛዝ ለማክበር ሲሉ ብቻ ከጠኗቸው አሽከሮች መካከል እየመረጡ ወደ ትምህርት ቤት መላካቸው፥ አስደማሚ ታሪካዊ ትዝታ ነው፡፡

"A History of Ethiopia in Pictures: from ancient to modern times" በሚለው መጽሃፋቸው ጂኦፍሪ ላስት፣ ሪቻርድ ፓንክረስት እና ኤሪክ ሮብሰን "[በ1917ዓ.ም.] እሳቸው [ንጉሡ] ተፈሪ መኮንን የተባለውን ትምህርት ቤት ከፈቱ። ከዚያም 'ማንም ኢትዮጵያን የሚወድ ትምህርት ቤቶችን ለማቋቋም ሊገድደው ይገባል' የሚል ዜና አስነግረዋል። በ1923ዓ.ም ደግሞ ንግሥቲቱ 'እቴጌ መነን' የተሰኘውን የልጃገረዶች ትምህርት ቤት አቋቋሙ። እንዲህ፣ እንዲህ እያለም የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ከቀድሞው በተሻለ ነገር ግን በአዝጋሚ ፍጥነት መጓዙን ቀጠለ።

በዚያን ወቅት የትምህርት መስጪያው ቋንቋ (በ1933ዓ.ም. በእንግሊዝኛ ከመተካቱ በፊት) ፈረንሳይኛ ነበር። ከ1904ዓ.ም. በኋላ በድሬዳዋና በአዲስ አበባ የአልያንስ ፍራንሴዝ ትምህርት ቤቶች መቋቋም፥ ይህን የፈረንሳይ ባሕላዊ የበላይነት ይበልጥ አጠናክሮታል። የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤትም ከ1923ዓ.ም. በፊት ለተማሪዎቹ የሚሰጠው የፈረንሳይ መንግስት ሠርቲፊኬት ፈተናዎችን ነበር። ከተጠቀሰው ጊዜ ወዲህ ግን ትምህርት ሚኒስቴር ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት ሆኖ በመቋቋሙ፥ በመጠኑም ቢሆን ኢትዮጵያዊ ቀለም ላላቸው ትምህርት ቤቶች መመስረት እና ትምህርት አሠጣጡንም ለኢትዮጵያውያን ተስማሚ እንዲሆን አስተዋፅዖ ማድረግ ጀመረ።

**ድኅረ ጣልያን**

ጣልያን ከኢትዮጵያ በሽንፈት ከተሰናበተችበት ከ1933ዓ.ም. በኋላ፥ ምንም እንኳን ሙሉ ለሙሉ የአገሪቱ የትምህርት ፍላጎት ሊረካ ባይችልም፥ በኢትዮጵያ የትምህርት ተቋሞች መጠነኛ እድገት ማሳየት ችለዋል። ባሕሩ ዘውዴ በጠቀስነው መጽሃፋቸው እንዳሰፈሩት በወቅቱ 700,000 የሚደርሱ ተማሪዎችን የሚያስተናግዱት "ትምህርት ቤቶች በሙሉ በመንግሥት የተቋቋሙ አልነበሩም። አያሌ የሚሲዮንና የግል ትምህርት ቤቶች ከመከፈታቸውም በላይ እያደር በሕዝቡ መዋጮ የሚሠሩት ትምህርት ቤቶች ቁጥርም እየተበራከተ" መጥቷል።

እንዲያም ሆኖ በጉልህ የሚስተዋሉ ፈተናዎች በትምህርቱ ዕድገት ላይ ተጋርጠው ነበር። የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶቹ አንፃር እጅግ ማነሱ እና የትምህርት ተቋሞች ስርጭት በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ መገደቡ ዋነኛ ፈተናዎች ነበሩ። አብዛኛዎቹ ትምህርት ቤቶች የተከፈቱት በኤርትራና መሃል አገር (ሸዋ አካባቢ) ነበር።

ከዚያ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም በአገሪቱ ይከፈቱ ጀመር። በወቅቱ ዝና ያተረፉት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጄኔራል ዊንጌት ናቸው።

ከፍተኛ ትምህርት በኢትዮጵያ የተጀመረው ደግሞ በ1943ዓ.ም. የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ኮሌጅ ሲመሰረት ነበር። ይህንን ተከትሎ በአምስት አመታት ውስጥ የመሃንዲስ ኮሌጅና የሕንፃ ኮሌጅ በአዲስ አበባ፣ የእርሻ ኮሌጅ በዓለማያ፣ የጤና ጥበቃ ኮሌጅ በጎንደር ተከፈቱ። በመጨረሻም እነዚህን ሁሉ በአንድ ጠቅልሎ እንዲያስተዳድር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩንቨርስቲ (የአሁኑ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ) ተመሰረተ።

እንደዚያም ሆኖ እስከ "አብዮቱ ፍንዳታ" ድረስ ፊደል የቆጠሩ ሰዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነበር። ከ1971ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ዓመታት የተካሔደው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ግን ፊደል የቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ቁጥር ከ8.8 በመቶ ወደ 50 በመቶ አሳድጎታል።

በ2001ዓ.ም. የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ መሠረት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ 23 የመንግስትና ከአርባ በላይ የግል ከፍተኛ ተቋማት የዲግሪ መርሐ-ግብር ትምህርቶችን እየሰጡ ይገኛሉ። በ2001ዓ.ም. 25,212 የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ)፣ 1,197 ሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ) ትምህርት ቤቶች እና 458 የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ማሰልጠኛ (TVET) ተቋማት በመላው አገሪቱ እንደሚገኙ የትምህርት ሚኒስቴሩ ዓመታዊ ስታትስቲክ አስፍሯል። በዚሁ ዓመት፥ በተማሪዎች ምዝገባ የግል ከፍተኛ ተቋማት ድርሻ 17.3% ነበር። በጥቅሉ በትምህርት ሽፋን ጥሩ ዕድገት እየተመዘገበ እንደሆነ ቁጥሩ ይናገራል።

## የምርምር ተቋማት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የምርምር ተቋም፥ አሁንም ድረስ የሰው እና የቁስ ሃብት እጥረት ችግሩ እንዳልተቀረፈ የሚነገርለት፣ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ስር በ1956ዓ.ም. የተመሰረተው የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም /Institute of Ethiopian Studies (IES)/ በመባል የሚታወቀው ተቋም ነው፡፡ ከዚያ በተሻገረ በምርምር ረገድ ኢትዮጵያ ዝናን ያተረፉ የምርምር (think-tank) ተቋማት አላፈራችም ለማለት ያስደፍራል፡፡ በርግጥ አንዳንድ መንግስታዊ ከሆኑ የምርምር ተቋማት ቀጥሎ፥ አሁን፣ አሁን ብቅ ጥልቅ የሚሉ መንግስታዊ ያልሆኑ የምርምር ተቋማትም አሉ፤ ከነዚህም መካከል በተለያዩ ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ የምርምር ዐውደ ጥናቶችን በማሰናዳት የሚታወቀው የማሕበራዊ ጥናት መድረክ/Forum for Social Studies (ማጥመ/FSS) ይገኝበታል፡፡

በሌላ በኩል ሳይጠቀሱ የማይታለፉት፥ ጥቂት የመንግስት (አዲስ አበባ፣ ጅማ፣ ሃሮማያ፣ መቀሌ እና ባሕርዳርን የመሳሰሉት) ዩንቨርስቲዎች ጎልቶ የወጣ ባይሆንም፥ ተስፋ ሰጪ ሊባል የሚችል የምርምር ስራዎችን እንደሚያካሒዱ ይታወቃል፡፡ ከግል ከፍተኛ ተቋማት መካከል ደግሞ በተለይ ዩኒቲ ዩንቨርስቲ እና ቅድስት ማርያም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ዘጠኝ እና ስምንት (እንደቅደም ተከተላቸው) ዓመታዊ፣ ብሔራዊ የምርምር ሥራዎችን በመደጎም እና ዐውደ ጥናቶችን በማካሔድ የግሉ የትምህርት ዘርፍም ለኢትዮጵያ ትምህርት እና ለምርምር ዕድገት ጉልህ እገዛ እንዲያደርግ የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ (ቅድስት ማርያም ዩንቨርስቲ ኮሌጅ በየዓመቱ የሚያዘጋጃቸው ዐውደ ጥናቶች በግል የከፍተኛ ትምህርት ዕድገት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፤ በተጨማሪም የተማሪዎች ምርምር መድረክን በማመቻቸት የመጀመሪያው ነው፡፡)

## ማሳረጊያ

ዘመናዊ ትምህርት በኢትዮጵያ አሁንም ድረስ የሚያኮራ ደረጃ እንዳልደረሰ የሚስማሙ ብዙዎች ናቸው፡፡ በመሠረቱ በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የተገኘ ዲግሪ በተለይም በምዕራቡ ዓለም ውስጥ በትምህርት ለመቀጠል ለሚፈልጉ ካልሆነ በቀር ለሥራ እምብዛም ተፈላጊነት የለውም፡፡ ይህም ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያንሳቸዋል ማለት ነው፡፡

ለጠቅላላው የትምህርት ዕድገት ከኢትዮጵያ፥ ትምህርት ሚኒስቴር በተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ (HERQA - በአዲሱ መዋቅር 'የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጫ ኤጀንሲ / ETQAA/')፣የከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል (HESC)፣ የሃገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት እና ሌሎቹም ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ በመታሰብ ተፈጥረዋል፡፡ የትምህርት ሽፋን በመላው ሃገሪቱ ይበል የሚያሰኝ ዕድገት እያሳየ ቢሆንም፥ የከፍተኛ ትምህርት በተለይም ከጥራት ጋር በተያያዘ ፈተናዎች ተጋርጠውበታል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚወጡ ምሩቃን ብቁ ተወዳዳሪ እንዳልሆኑ በብቃት ማረጋገጫ ፈተናዎች ሳይቀር እየተስተዋለ ነው፡፡ ችግሩ የመንግሥት ተቋማት ምሩቃንንም የሚመለከቱ ናቸው፡፡

የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሃገር አቀፍ ፈተናዎች ላይ የሚያስመዘግቡት ውጤት ከመንግስት ተማሪዎች ውጤት እጅግ የላቀ ነው፡፡ ጎልተው እየወጡ ያሉት አንዳንድ የግል ከፍተኛ ተቋማትም ይህንኑ እውነታ በመንግሥት ዩኒቨርስቲዎች ላይ ወደሚደግሙበት አቅም እየገሰገሱ መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ አሁን እንደተጓደለ ለታመነበት የጥራት ችግር መፍትሄው በኢትዮጵያ ትምህርት ጥራት እና ዕድገት ላይ የምርምር ሥራዎችን እየሰሩ የማጎልበቻ ብልሐት የሚጠቁሙ አካላትን መፍጠር ወይም የተፈጠሩትን ማበረታታት ብቻ ነው፡፡

### ዋቢ ንባቦች፡-


Accessed on January 30, 2011. *http://www.chatham.edu/pti/curriculum/units/2004/Renne.pdf*

Accessed on January 30, 2011. *http://www.higher.edu.et*

Accessed on November 20, 2010. *http://www.fssethiopia.org.et*

FDRE, MoE. March 2010. *Educational Statistic: Annual abstract 2001E.C.*

Geoffrey Last, Richard Pankhrust and Eric Robson. 2010. ***A History of Ethiopia in Pictures: from ancient to modern times***

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ 2002ዓ.ም፤ ***የኢትዮጵያ ታሪክ፡- ከ1847 እስከ 1983ዓ.ም.***

ተክለፃዴቅ መኩሪያ:: 1981ዓ.ም. ፤ ***አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት፡፡***

ጳውሎስ ኞኞ፡፡ 1981ዓ.ም. ፤ ***አጤ ምኒልክ፡፡***